## የመሥራት ፕሮግራም ተሳታፊዎች የፈቃደኝነት መግለጫ ቅጽ

**ገበያ ዴቨሎፐርስ አገልግሎት ሰጭ ኃ/የተ/ የግል ማኅበር** ፕሮግራሞቹን ምንጊዜም የተሻሉ በማድረግ በተሳታፊዎቹ ላይ አወንታዊ ተጽዕኖ ለማምጣት በቁርጠኝነት እየሰራ ይገኛል። ይህን ዓላማ ለማሳካት፣ ስለ ፕሮግራሙ ተስታፊዎች መረጃ በመሰብሰብ ትንታኔ ያከናዉናል። የግል መረጃዎን ምስጢራዊነትን ለመጠበቅ ከፍ ያለ ዋጋ እንሰጣለን። ይህ የፈቃደኝነት መግለጫ ቅጽ በመሥራት ፕሮግራም ውስጥ የግል መረጃዎን በምን መልኩ እንደምንሰበስብ፣ እንደምንጠቀምና እንደምናጋራ የሚያስረዳ ነው። እባክዎ ቅጹን በጥንቃቄ አንብበው፣ መስማማትዎን በፊርማዎ ያረጋግጡ።

**ውሳኔ ላይ ከመድረስዎ በፊት እባክዎ ይህንን ቅጽ በጥንቃቄ ያንብቡ።**

**የፕሮግራሙ ስም:** *መሥራት*

**መረጃ ሰብሳቢ:** ገበያ ዴቨሎፐርስ አገግሎት ሰጪ ኃ/የተ/ የግል ማኅበር፤ አድራሻ፣ ቂርቆስ ክፍለ ከተማ፣ ወረዳ 9፣ የቤት ቁጥር 501/004/498፣ 14ኛ ፎቅ፣ አዲስ አበባ

### 1. የመረጃ መሰብሰብ ዓላማና ጠቀሜታ

የግል መረጃዎን የምንሰበስበው በፕሮግራሙ ሂደት ውስጥ የመጣውን ለውጥ ለመገምገም፣ እንዲሁም ከሚሰበሰበው መረጃ በመነሣት ፕሮግራሙን ለማሻሻል ነው። ይህም የመሥራት ፕሮግራምን ውጤታማነት ለመከታተልና ለመመዘን፣ እንዲሁም ወደ ፊት ፕሮግራሙን ሊቀላቀሉ ለሚችሉ ተሳታፊዎች ፕሮግራሙን የተሻለ ማድረግ የሚቻልባቸውን መንገዶች መጠቆም ያካትታል።

### 2. የሚሰበሰበው መረጃ ምንድን ነው?

ስለ እርስዎ የሚከተሉትን መረጃዎች ባጠቃላይ ወይም በከፊል ልንሰበስብ እንችላለን:

- ስም፣ ዕድሜ እና ጾታ
- ስልክ ቁጥር፣ መገኛ አካባቢ፣ የቤት አድራሻ እና ኢሜይል
- በፕሮግራሙ ውስጥ ያለዎት ተሳትፎ ዝርዝር መግለጫ (የተጠቀሙት አገልግሎት ዓይነት)
- የትምህርት ደረጃ
- የትዳር ሁኔታ
- ስደተኛ፣ ከስደት ተመላሽ ወይም ተፈናቃይ መሆንዎ ወይም አለመሆንዎ
- የአካል ጉዳት መኖር አለመኖሩ
- የሥራ ሁኔታ እና ዓይነት
- ለዳሰሳ ጥናት መጠይቅ የሰጧቸው ምላሾች

### 3. መረጃዎን የምናጋራው ለማን ነው?

*መረጃዎን ለሚከተሉት አካላት ልናጋራ እንችላለን:*

- ማስተርካርድ ፋውንዴሽን
- ለምዘና እና ግምገማ ሥራ ማስተርካርድ ፋውንዴሽን ሊቀጥራቸው ለሚችሉ ሦስተኛ ወገን መረጃ ተንታኞች (ለምሳሌ፣ የመረጃ ጥንቅርና ትንተና ሥራ የሚሠሩ ድርጅቶች)
- ገበያ ዴቨሎፐርስ አገልግሎት ሰጭ ኃላ/የተ/የግል ማኅበር የግል መረጃን በምን መልኩ እንደሚጠቀም ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እባክዎ https://gebeya.com/privacy-policy/ን በመጎብኘት የግል መረጃ ፖሊሲያችንን ይመልከቱ። የማስተርካርድ ፋውንዴሽን የግል መረጃ ፖሊሲ ደግሞ https://mastercardfdn.org/privacy/ ላይ ያገኛሉ።

### 4. የእርስዎ መብቶች:

*መረጃ ለማጋራት ፈቃደኛ የመሆን ግዴታ የለብዎትም። መረጃ ለማጋራትም ሆነ ላለማጋራት ቢወስኑ፣ በሁሉም የፕሮግራሙ ሂደቶች ውስጥ ሊሳተፉ ይችላሉ። መረጃ ለማካፈል ፈቃደኛ የመሆን ጉዳይ በምንም መልኩ ከፕሮግራሙ ተሳታፊነት ጋር አይያያዝም። የግል መረጃዎን በተመለከተ የሚከተሉት መብቶች አሉዎት:*

- ***መረጃውን የማግኘት መብት:*** *ስለ እርስዎ ያለንን መረጃ ቅጅ ላግኝ ብለው የመጠየቅ መብት አለዎት።*
- ***መረጃውን የማስተካከል መብት:*** *ስለ እርስዎ ያለንን የትኛውንም የተዛባ መረጃ እንድናስተካክል የመጠየቅ መብት አለዎት።*
- ***መረጃው እንዲጠፋ የመጠየቅ መብት:*** *መረጃዎ እንዲወገድ የመጠየቅ መብት አለዎት።*
- ***መረጃ ጥንቅር እንዳይደረግ የማድረግ መብት:*** *መረጃዎ እንደ ግብዓት ተወስዶ ጥንቅር እንዳይሠራበት የመጠየቅ መብት አለዎት።*
- ***መረጃ ጥንቅርን የመቃወም መብት:*** *መረጃዎ ላይ ጥንቅር እንዳይካሄድ የመቃወም መብት አለዎት።*
- ***የመረጃ ዝውውር መብት:*** *መረጃዎ ለሌላ ድርጅት ተዘዋውሮ እንዲሰጥ የመጠየቅ መብት አለዎት።*

### 5. ፈቃደኝነትዎን የመሰረዝ መብት:

*መረጃዎን የማካፈል ፈቃደኝነትዎን በየትኛውም ጊዜ የመሰረዝ መብት አለዎት። ይህንን ማድረግዎ፣ በፕሮግራሙ ውስጥ ያለዎት ተሳታፊነት ላይ ምንም ዓይነት ተጽዕኖ የለውም። ፈቃደኝነትዎን ለመሰረዝ በኢሜይል አድራሻችን* mesirat@gebeya.com *ያግኙን።*

### 6. ምርጫዎ ያለውን ዋጋ ማወቅ:

*መረጃዎን ለማጋራት ፈቃደኛ በመሆንዎ፣ እርስዎንም ሆነ የወደፊት የፕሮግራሙ ተሳታፊዎችን በመደገፍ መሥራት ፕሮግራም ስኬታማ እንዲሆን እያገዙ ነው።*

***ለገበያ ዴቨሎፐርስ አገልግሎት ሰጭ ኃላ/የተ/ የግል ማኅበር እና ማስተርካርድ ፋውንዴሽን፣ እንዲሁም ከላይ ለተገለጸው ዓላማ ሲባል መረጃውን ሊያጋሯቸው ለሚችሉ ሦስተኛ ወገን መረጃ ተንታኞች መረጃዬን ለማጋራት ተስማምቻለሁ።***

- *የተሳታፊ ስም:* ______________________________
- *የተሳታፊ ፊርማ:* ______________________________
- *ቀን:* ______________________________

**እባክዎ የዚህን ቅጽ ቅጅ ለራስዎ ይያዙ።**